# Emmanuel Development Association

## አማኑኤል የልማት ድርጅት

# አድራሻ


አማኑኤል የልማት ድርጅት

ዋናው ቢሮ
የመ.ሳ.ቁ 908
ስልክ +251 11 6 461426
+251 11 6 460188
ፋክስ + 251 11 6 460199

ኢሜይል፡-emmanuel.eth@ethionet.et
ዌብሳይት፡- www.edaethiopia.org

አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ



የአቃቂ አካባቢ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት

ስልክ +251 11 4 347670
ፋክስ + 251 11 6 460199
ኢሜይል፡-edacentral@gmail.com
የመ.ሳ.ቁ 908

አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ



Emmanuel Development Association

አማኑኤል የልማት ድርጅት


# በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚፈፀም የወሲብ ጥቃት



## ሴቶች ላይ የሚፈፀም ፆታዊ ጥቃት ማለት ምን ማለት ነው?

1

በሴቶች ላይ የሚፈፀም ፆታዊ ጥቃት ማለት በሴቶች ላይ ማንኛውም አይነት አካላዊ፡ ስነ ልቦናዊና ወሲባዊ ጉዳት የሚያደርሱ ጥቃቶችንና የተያያዙ ማስፈራሪያዎችን፡ የነፃነት መነፈጎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡

ማንኛውም በሴቶች ላይ የሚፈጸም ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መነሻ በማህበረሰቡ ውስጥ በፆታዎች መካከል ያለው የሀይል መዛባት ውጤት ነው፡፡ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሴቶችን ለተደራራቢና ለማያቋርጥ ጭቆና ይዳርጋል፡፡

ፆታዊ ጥቃት ዕድሜ፡ ሀይማኖት፡ የኑሮ ደረጃ የመኖሪያ ስፍራና የመሳሰሉትን ሳይለይ በሁሉም ሴት ላይ ሊከሰት ይችላል፡፡ ሴቶች በቤታቸውም ሆነ ከቤታቸው ውጭ የፆታዊ ጥቃት ለሰባ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## የቤት ውስጥ ጥቃት ምንድን ነው?

2

ቤተሰብ ለሁሉም በተለይም ደግሞ ለሕፃናት ዕድገት፣ ደህንነትና ጥበቃ ምቹ የሆነ ቦታ ነው፡፡ ነገር ግን በዓለም ዙሪያ ላሉ አብዛኞቹ ሕፃናት ቤታቸው ራሱ አደገኛ ቦታ ይሆንባቸዋል፡፡ በቤተሰበ ያለ የኃይል ጥቃት አብዛኛውን ጊዜ የተሰወረ ነው፡፡

የቤት ውስጥ ጥቃት በተለያየ መልክ ይገለፃል፡፡ የቤት ውስጥ ጥቃት ግንኙነት ወይም ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል አንደኛው በሌላው ላይ ተፅእኖ ለማድረግ የበላይነትን ስልጣኑን የሚገልፅበት ወይም ጥቃት የሚደርስበት ድርጊት ነው፡፡ ወላጆች፣ የእንጀራ እናቶች ወይም አባቶች፣ ወንድሞች ወይም እህቶች፣ ዘመዶች እና ሌሎች ሕፃናትን የሚንከባከቡ ሁሉ በቤት ውስጥ የኃይል ጥቃትን በተለያየ መልኩ ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡



በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚፈፀም የወሲብ ጥቃት

- ለህገ ወጥ ውርጃ ወይም በወሊድ ሳቢያ ለሞት መዳረግ
- በመደፈሯ ከትምህርት ወይም ከስራዋ መደናቀፍ
- በመደፈሯ ቤተሰቦቿ ወይም ህብረተሰቡ በአጠቃላይ እራሷን ጥፋተኛ ማድረግና ማግለል
- ተስፋ በመቁረጥ ወደ ሴተኛ አዳሪነት ህይወት መግባት ወዘተ.

ህፃናት ገና ለጋ ታዳጊ በመሆናቸው እራሳቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ አቅም ያንሳቸዋል፡፡ በመሆኑም ለተለያዩ ብዝበዛዎችና ጥቃቶች የተጋለጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሌሎች አዋቂዎች እገዛ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ህፃናትን እንዲጠበቁ አደራ የሚጣልባቸው ሰዎች ባህሪን ጠንቅቆ ማወቅ የወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ኃላፊነትና ግዴታ መሆን ይኖርበታል፡፡

ህፃናት የወደፊቱ የሀገርና የወገን ተስፋ ናቸው፡፡ በእነርሱ ላይ የሚደርሰውን ወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ ዝም ብሎ መመልከት ድርጊቱን ከሚፈፅሙት ወንጀለኞች የሚለየን አይሆንም፡፡ ስለሆነም ያለውን ችግር ለመቅረፍ ወደፊት የሚደርሰውን ለመከላከልና ብሎም ለመቆጣጠር ህብረተሰቡ የወሲብ ጥቃትና ብዝበዛ የሚፈፅሙ ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አስፈላጊውን ጥቆማ ለህግ አስከባሪዎች በመስጠት መተባበር ይጠበቅበታል፡፡

Emmanuel Development Association

በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚፈፀም የወሲብ ጥቃት

## 3 በህፃናት ላይ በቤት ውስጥ የሚደርሱ ጥቃቶች

በሕፃናት አካል ላይ የሚደረጉ አብዛኞቹ የኃይል ጥቃቶች ለሞት ወይም ለረጅም ጉዜ ጉዳት አይዳርጉም:: አብዛኛውን ጊዜ ሕፃናት ስነ ሥርዓት እንዲይዙ በሚል የሚደረግ ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በጣም ለጋ በሆኑ ሕፃናት ላይ ከደረሰ የጤና ችግሮችን ብሎም ሞትን ያመጣል:: ለምሳሌ በጣም ለጋ ሕፃንን በኃይል መወዝቀዝ ለአእምሮ ጉዳት ወይም ለሞት ሊዳርግ ይችላል::

ቤተሰቦች አብዛኛውን ጊዜ ስሜታዊ የኃይል ጥቃትን ወይም የአካል ቅጣትን ይጠቀማሉ:: ማሳዘን፣ ተቀጽላ ስም መስጠት፣ ዛቻዎች፣ ሕፃናትን መለየትና ማግለል ሁሉ የሐይል ጥቃት መልኮች ናቸው:: በዓለም ላይ በቤተሰብ ውስጥ በሕፃናት አካል ላይ የሚፈጸም ቅጣትን ፈጽሞ የሚከለከል ሕግ ያለንቸ ው 16 አገሮች ብቻ ናቸው::

ህፃናትን ቸል ማለትና ተገቢውን እንክብካቤ መንፈግ ሌላው በህፃናት ላይ በቤተሰብ የሚፈፀም ጥቃት ወይም በደል ነው:: ቤተሰቦች ሕፃናት በጤና እንዲሁም ከአደጋ በመጠበቅ ማደጋቸውን አያረጋግጡም፣ እንዲሁም ከአደጋም አይጠብቋቸውም:: ሴቶችና የአካል ጉዳተኛ ሕፃናት አብዛኛውን ጊዜ የመገለል አደጋ የተጋለጡ ናቸው::

ሕፃናት በቤተሰባቸው ውስጥ ባሉበት ወሲብ እንዲፈፅሙ የሚገደዱባቸው አጋጣሚዎች አሉ:: ህጻናት በማይመቻቸው እና ደስ በማይላቸው መልኩ የመነካካትና የመጎንተል ጥቃት ብሎም አስገድዶ የመደፈር ጥቃት በቤተሰብ ውስጥ በሚገኙ ወንዶች ሊደርስባቸው ይችላል:: ከ1 እስከ 21 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች የ15 ዓመት ዕድሜ ላይ ሲደርሱ የወሲብ ጥቃት ተጎጂ ይሆናሉ::ከዚህ ባሻገር 82 ሚሊዮን የሚሆኑ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሴቶች የ18 ዓመት እድሜ ላይሞላቸው ጋብቻ ይፈፅማሉ ::

አብዛኞቹ ከ18 ዓመት እድሜ በታች ቢሆኑም አዛውንት የሆኑ ግለሰቦችንም ለማግበት ይገደዳሉ:: በዚህም ምክንያት የኃይል ጥቃት እንዲሁም አለፈቃዳቸው ወሲብ እንዲፈፅሙ ይገደዳሉ::

## 4 ከጥቃት ነፃ የሆኑ ቤተሰቦች እንዲኖሩ ምን ማድረግ ይገባል?

ብዙውን ጊዜ የኃይል ጥቃት የሚከሰተው ወላጆች ሕፃናትን ለማስተማርና ለማሳደግ አስፈለጊ ነው ብለው ስለሚያምኑ እና ስለሚያስቡ፣ ወይም ሌሎች የማስተማሪያ አማራጮችን ስለማያውቁ ነው::

ወላጆች ሁልጊዜም ሕፃናቶችን ለማሳደግ ዋናውን ሃላፊነት መቀበል ይገባቸዋል:: ይሁን እንጂ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህን ለማድረግ እንዲችሉ የሚከተሉትን ነገሮች በማድረግ ማገዝ ይኖርባቸዋል::

ወላጆችና ሌሎች ተንከባካቢዎች በቂ ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው:: ለዚህም ጥሩ የጤና እንክብካቤና ትምህርት እንዲሁም አዋቂዎች ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ በቂ ገንዘብ እንዲኖራቸው ስራ እንዲያገኙ አልያም በአንዳች አይነት የገቢ ማስገኛ መስክ ላይ እንዲሰማሩ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል::

የተለየ ችግር ላለባቸውን ቤተሰቦች ተጨማሪ ዕርዳታ መስጠት ያስፈልጋል:: ለምሳሌ:- በተለያየ ምክንያት ወላጆቻቸውነ ያጡ ወይም አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሕፃናትን ለሚንከባከቡ ቤተሰቦች ተጨማሪ ዕርዳታ መስጠት ያስፈልጋል::

ለቤተሰቦች በቂ ዕርዳታ፣ ምክርና መረጃ በመስጠት ከጥቃት ነፃ የሆኑ ቤተሰቦች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣ ወላጆች እናቶችና አባቶች ግጭቶችን በአዎንታዊ መንገድ ስለመፍታት እንዲሁም በሴቶችና በወንዶች መካከል የፆታ መበላለጥ እንደሌለ በቂ ትምህርት ማግኘት መቻል ይኖርባቸዋል:: እንዲሁም ስለ ሕፃናት የእድገት ሂደትና እድሜያቸውም እየጨመረ ሲመጣ አመለካከቶቻቸውን ማክበር አስፈላጊ ነገር መሆኑን ወላጆች መማር አለባቸው::


Emmanuel Development Association

## 5 በሴት ህፃናት ላይ የሚደርሱ ወሲባዊ ጥቃቶች

በተለያዩ ተፅእኖዎች ምክንያት በሴት ህፃናት ላይ በርካታ የሆኑ አካላዊና ስነ አእምሮአዊ በደሎችና የወሲብ ጥቃቶች ይደርሱባቸዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹም

- አዋቂዎች አስገድደው የሚፈፅሙት  የወሲብ ጥቃት
- የቤተሰብና የራሳቸውን ኑሮ ለመደጎም ሲሉ በየመጠጥ ቤቶች ቆሎ ሲጃራ ፓስቲ ወዘተ ለሽያጭ የሚያዞሩ ሴት ህፃናት በጠጪዎች /በሰካራሞችና በመጠጥ ቤት ባለቤቶች/ ለወሲብ ጥቃትና ብዝበዛ ይገፋፋሉ እምቢተኛነታቸውን ከገለፁም ይሰዳባሉ ይመታሉ ይደፈራሉ፡፡
- በትምህርት ቤት አካባቢ በሱስ የተጠመዱ ወጣቶች ሴት ተማሪ ህፃናትን በማስገደድ የወሲብ ጥቃት ይፈፅሙባቸዋል፡፡
- የቤት ሰራተኛ የሆኑ ሴት ህፃናት በቀጣሪዎቻቸው ወይም በሌሎች አዋቂዎች ወሲባዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡
- ህፃናት በቤተሰቦቻቸው ቤት ወስጥም ሆነው ለወሲባዊ ጥቃት የሚጋለጡባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡

## 6 ህፃናትን ለወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ የሚያጋልጡዋቸው መንስዔዎች

ሴት ህፃናትን ለወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ የሚገፋፉዋቸው ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ግን የሚከተሉት ናቸው፡፡



በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚፈፀም የወሲብ ጥቃት

***ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፡-*** ህፃናት ቤተሰቦቻቸውን በኢኮኖሚ ለመደገፍ ሲሉ በጎዳና ላይ ለመስራት ይገደዳሉ፡፡ በመሆኑም ለጥቃትና ለወሲባዊ ብዝበዛ ይጋለጣሉ፡፡

***የቤተሰብ መፍረስ፡-*** እናትና አባት ወይም አንዳቸውን ባመጣት እንዲሁም አስተዳዳሪና ደጋፊ በማጣት ህፃናት ለጎዳና ህይወት ይዳረጋሉ፡፡ ይህም ለወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ ያጋልጣቸዋል፡፡

***የቤተሰብ ተፅዕኖ፡-*** ቤተሰቦች በሚያጋጥሙዋቸው ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያ ችግሮች ሳቢያ እንዲሁም ባለው ኋላቀር ልማዳዊ አስተሳሰብ የተነሳ ሴት ልጆቻቸውን ማስተማር ማስተዳደርና መንከባከብ ሲያቅታቸው በወሲባዊ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ገንዘብ እንዲያመጡ ይገፋፉዋቸዋል፡፡

***ከኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ጋር የመጣ አንድ አስተሳሰብ:*** ይህውም ህፃናት በዚህ በሽታ የመጠቃት እድላቸው አነስተኛ ነው በሚል እምነት ህፃናትን ለዝሙት ተግባር የመምረጥ አዝማሚያ እየጨመረ መምጣት ነው፡፡

## 7 በግዳጅ መደፈር በህፃናት ላይ የሚያስከትላቸው ችግሮች

- ስነ ልቦናንና አእምሮ ጤናን በተመለከተ መደንዘዝ ግራ መጋባት እንደገና ጤናማ አልሆንም ብሎ ማሰብ ደስተኛ አለመሆን ተስፋ መቁረጥ ወዘተ.
- የደፈራት ሰው በኤች አይ ቪ ወይም በሌላ የአባላዘር በሽታ የተያዘ ከሆን እነዚህ በሽታዎች መያዝ

Emmanuel Development Association